homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
ስልክ ቁ፡- 1300 650 172
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

ለዚህ ቤት ኗሪዎች፣

**በታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) የመልሶ ግንባታ ፕሮግራም ላይ የሚደረግ ጠቃሚ ማሻሻያ**

ሆምስ ቪክቶሪያ በሴፕቴምበር 2023 ለነዋሪዎች የተሻሉ ቤቶችን ለማቅረብ የታወጀውን የታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) የመልሶ ግንባታ ፕሮግራም ያለውን ለውጥ ለማሳወቅ እየጻፈልዎት ነው።

እንደ የታላቁ የመኖሪያ ቤት ግንባታ (Big Housing Build) አካል፣ የቪክቶሪያ መንግስት በሜልበርን ዙሪያ ያሉ የቆዩ ሰማይ ጠቀስ የማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች መልሶ ለመገንባት ቀጣዩን ትልቅ እርምጃ እየወሰደ ነው።

## ዛሬ የታወጀው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ በሚከተሉት ህንፃዎች ውስጥ ያሉ ነዋሪዎችን ወደ ሌላ ቦታ የማዛወር እቅዳቸው በቅርቡ እንደሚጀመር እና እስከ ፌብሩዋሪ 2026 ድረስ እንደሚጠናቀቅ አሳውቀናል፡-

- 259 Malvern Road, South Yarra
- 139 Highett Street, Richmond
- 111, 119 & 127 Elizabeth Street, Richmond
- 6 & 8 Anderson Court, Richmond
- 1-5, 7 & 9 Williams Court, Richmond.

## ለፍሌሚንግተን እና ሰሜን ሜልቦርን የመዛወሪያ ማብቂያ ቀን ተገለጿል

እንዲሁም በ2023 መገባደጃ ላይ የመዛወር እቅድ የጀመሩ በሚከተሉት ህንፃዎች ውስጥ ያሉ ነዋሪዎችን መዛወራቸው እስከ ሴፕቴምበር 2025 ድረስ እንደሚጠናቀቅ አሳውቀናቸዋል፡-

- 120 Racecourse Road, Flemington
- 12 Holland Court, Flemington
- 33 Alfred Street, North Melbourne

## ከጁላይ 2026 በፊት የሚጀመር ሌላ የሰማይ ጠቀስ ህንጻዎች ዝውውር የለም

ከጁላይ 2026 በፊት ለሚደረጉ የሰማይ ጠቀስ ፎቆች ዝውውር ተጨማሪ ይፋ የሚደረግ ነገር አለ ብለን አንገምትም። ከቤትዎ ማዛወር መቼ እንደሚጀመር ለማሳወቅ ከእርስዎ ጋር መገናኘታችንን (መነጋገራችንን) እንቀጥላለን።

## መረጃ ይኑርዎት ደግሞም ግንኙነት አያቋሙ

በቋንቋዎ ጨምሮ ስለ መልሶ ግንባታው እና የመዛወር ሂደት መረጃ ለማግኘት bighousingbuild.homes.vic.gov.auን መጎብኘት ይችላሉ። ለመደበኛው የመረጃ ወቅታዊነት እና ማስጠንቀቂያዎች በመመዝገብ ከነገሩ ሳይርቁ (እንደተገናኙ) መቆየት ይችላሉ።

ቦታውን እንዲጎበኙ፣ የአከባቢዎ የቤቶች ቢሮ ጋር እንዲነጋገሩ፣ የመረጃ ክፍለ ጊዜ እንዲከታተሉ እና ከእኛ ጋር እንዲገናኙ እናበረታታዎታለን።

የከበረ ሰላምታ

**Dannii de Kretser**
*ጊዜያዊ ስራ አስከያጅ፣ ሆምስ ቪክቶሪያ*

Amharic | አማርኛ

VICTORIA State Government